# የተቃዋሚዎቻችን የአዲስ ዓመት በረከት ... "መተያየት"

## *«መፈወስ ለራስ ንስሃ ከመግባት እና ራስን እውን ከማድረግ ይጀምራል፡፡»*

**(ቶማስ ፍሬድማን፣ ዘ ወርልድ ኢዝ ፍላት፣ ገፅ 406)**

ለዴሞክራሲ ስር ይዞ መቀጠል ዋናው መሰረትና ዋስትና ስርዓታዊ አዋጅና ፈቃደኝነት አይደለም፡፡ ይህ ያለው አስተዋፅኦ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋነኛው ህብረተሰብ ባጠቃላይ እና ምሁራኑና የፖለቲካ ልሂቃኑ በተለይ በተናጠልና በጋራ የተሸከሙትን ማንነት፣ የትላንት ታሪክና የዛሬ ድርጊት ገላልጦ ለማየት፣ በሰለጠነ መንገድም እየነቀሱ ለመውቀስም ሆነ ለማወደስ የሚደፍር ባህሪና ባህል ባለቤት መሆናቸው ነው፡፡

በአጭሩ የዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብና አመለካከት ባለሃብትና ባለቤት መሆን ማለት ነው፡፡ ባለፉት 14 ዓመታት ሁላችንም እንደ ህብረተሰብ፣ በተለይ ደግሞ የተቃዋሚ ፓርቲዎቻችን የገዘፈ ቡድናዊ እጥረት ሆኖ ያየነው ግብዓትም ይኸው ነው፡፡ በተቃራኒው ሳይተዋወቁ መተቃቀፍ፣ ቢተዋወቁም ተሸፋፍነውና ተቀናቃኞችን ደስ እንዳይሰኝ በሚል ፈሊጥ ሳይነካኩ ለመጓዝ ተቃዋሚዎቻችን የሞከሩት ሙከራ ብቸኛ ውጤት የማያስቀሩት የጓዳ ማኩረፍ ሆኖ ጀማሪ ዴሞክራሲያችንን የጎዳ አሳፋሪ መራኮትና መጓተት ጭኖብን አይተናል፡፡

እነሆ የከፋ መወሻሸት ካየንበት የምርጫ 97 ማግስት ወዲህ ብቅ ጥልቅ እያለች የከረመችው እውነተኛ ማንነትን የማየትና የመተያየት ጀምበር በቋሚነት ልታሞቀን ከእለት እለት ቀጥላ መታየትን እያስለመደችን ይመስላል፡፡ ይህን ሳጤነው በእርግጥም ቀስ በቀስ ተቃዋሚዎቻችን ከአደንዛዥ ማስታገሻዎች ዘላቂ መፍትሔ አለመሆን ተምረው ወደ ፈውስ ጎዳና የመመለሱን እርምጃ ጀመሩ ለማለት ያስደፍራል፡፡ የተቃዋሚዎቻችን የአዲስ ዓመት በረከት ያልነውም ይህንኑ እንዲያዘልቅልን ካለን ፅኑ ምኞት ነው፡፡

የዚህ የፈውስ ጉዞ ጅማሮ ጥሩ ዋቢ ሆነው ያገኘናቸውን የተቃዋሚዎቻችን ገለፃ እንጥቀስ፡፡ የኢዴአፓ መድህን መሪ ክቡር አቶ ልደቱ አያሌው፣ በክቡር በየነ ጴጥሮስ የሚመራው የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኅብረት እንዲሁም በእነ አቶ ተስፋዬ ቶሎሳ የሚመራው የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ ካወጧቸው ፅሑፎች ያገኘነው እንደሚከተለው ተቀንጭቦ ቀርቧል፡፡

**ክቡር አቶ ልደቱ አያሌው በዶ/ር ብርሃኑ ነጋ መፅሐፍ ላይ ካቀረቡት (ሪፖርተር ጋዜጣ፣ ገፅ 37 እና 42)**

**«... የቅንጅቱን አጠቃላይ ሂደት በሚመለከት መፅሐፉ በርካታ መረጃዎችንና ሐቆችን ያካተተ መሆኑን መካድ ባይቻልም በዚያው መጠን በጣም በርካታ ተዛብተው፣ ተጣመው፣ ተጋነው፣ ተቀንሰው፣ ተጨምረው፣ ከዚያም በላይ በሐሰት የቀረቡ ሃሳቦችን ያካተተ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ... የቀድሞ የኢህአፓና የመኢሶን አባላት ከ20 ዓመት በኋላ ስለ ድርጅቶቻቸው ታሪክ የፃፏቸውን መፅሐፍት ሳነብ በሁለት ድርጅቶች መካከል የሚታየው የታሪክ ባለቤትነት ሽሚያ በጣም አድርጎ ያስገርመኝ ነበር። ነገር ግን የምርጫ 97ዓ.ም ትዝታ ከህሊናችን ገና መደብዘዝ ባልጀመረበት በአሁኑ ወቅት ትግሉን ከተቀላቀሉ ገና አንድ ዓመት ያልሞላቸው ዶ/ር ብርሃኑ የሁሉም የትግል ታሪክ ባለቤት እርሳቸውና ቀስተ ደመና መሆናቸውን ሊነግሩን መድፈራቸውን ሳይ የኢህአፓና የመኢሶን ታሪክ ፀሐፊዎችን በልቤ ማሩኝ ብያቸዋለሁ።... ዶ/ር ብርሃኑ ቅንጅት ይዞት የቀረበው ራዕይ የማን ነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ሲሞክሩ እውነቱን ... ባይፈልጉ እንኳ ቢያንስ የቅንጅቱ ራዕይ የጋራችን ነው ብለው ቢፅፉ በተወሰነ ደረጃ የጨዋ አባባል ይሆን ነበር። ...»**

**ከደኢሕዴን ሥ/አ/ኮ መግለጫ (መስከረም 13፣ 1999)**

**«... ደኢሕዴን በዐቅሙ ክልል የተያያዘውን ትግል ከመቀጠል አልፎ ሌላ የፖለቲካ ድርጅትን ለስልጣን የማብቃት አጀንዳ ይዞ እንደማይሄድ ግልፅ ሆኖ እያለ፤ ፓርላማ የመግባት የራሱን ውሳኔ ለምን አደረገ የሚሉ ወገኖች ቢኖሩ በእጅጉ ተሳስተዋል...። ... ድርጅቶች አንዱ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) የተባለው ድርጅት የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ሕብረት አባላትን ለመከፋፈልና ሞራለ ደካማ የሆኑትን ደግሞ በመሳሪያነት ለመጠቀም በተደጋጋሚ ሲያደርግ የቆየው ሙከራ ሳይሳካለት ሲቀር በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአስነዋሪ ተግባሩ በመግፋትና በይሉኝታ ቢስነት በግልፅ በሀገር ውስጥና በውጭ በሚያሰራጫቸው በራዲዮ ጣቢያዎቹ አማካይነት የደኢሕዴንና የመሪዎቹን ስምና ክብር በሚያጎድፉ የበሬ ወለደ ውሸት ዘመቻ እያካሄደ ይገኛል።**

**... የሰሜን አሜሪካ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እ.ኤ.አ ኦገስት 27 2006 በዋሽንግተን ለአባላቱና ለደጋፊዎቹ የጠራውን ሕዝባዊ ስብሰባ ለማደናቀፍ ከአንድ ዴሞክራት ነኝ ከሚል**

ድርጅት የማይጠበቅ ርካሽ ተግባራትን ሲፈፅም በበቂ መረጃ ማረጋገጥ ችለናል፡፡ ሕዝቡ ወደ ስብሰባው እንዳይመጣና የሚመጡትንም ወደ ስብሰባው እንዳይገቡ በዚህም ሳይበቃ በስብሰባው ዕለት ማንነታቸው በሚገባ የሚታወቁ አባሎቹንና ደጋፊዎቹን በማሰማራት ወደ ስብሰባው የሚመጡ ... የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ተወላጆችና ሌሎች ኢትዮጵያዊያንን ሁሉ ክብር የሚነካ ፀያፍ ስድቦች ... ሲያውክ ውሏል፡፡ ... ኢሕአፓና መሰሎቹ ... ጊዜአቸውን ከማባከን ይልቅ በራሳቸው ድርጅታዊ ስራ ላይ እንዲያተኩሩና በተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከልም ሆነ በአጠቃላይ በሀገራችን እንዲለመድና እንዲዳብር በምንታገለው የመቻቻል ፖለቲካ ባህል ላይ አፍራሽ ድርጊቶችን ከመፈፀም እንዲቆጠቡ የደኢሕዴን ሥ/አ/ኮ በጥብቅ ያሳስባል፡፡ ... ዴኢሕዴን ድርጅታዊ ነፃነቱንና የሚወክላቸውን የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች መብትና ክብር ለማስጠበቅ በሚወስዳቸው ቀጣይ እርምጃዎች ሁሉ ለሚከተለው ሁኔታ ትንኮሳውን እየፈፀሙ ያሉት ኢሕአፓና መሰሎቹ ሙሉ ተጠያቂ እንደሚሆኑ ያስገነዝባል፡፡ ...»

**ከኦብኮ ሥ/አ/ኮ መግለጫ (መስከረም 13፣ 1999)**

«... 1997ዓ.ም አገር አቀፍና ክልላዊ ምርጫ ... የብዙ ወገኖች የተደበቀ አጀንዳም ይፋ የሆነበት ... ነበር፡፡ ... ከአሁን በኋላ እሽኮኮ የምንሸከምበት ወቅት ያበቃ መሆኑን በአንክሮ እያሳሰብን ታሪካዊ ኃላፊነቱን በማይወጡትና ወደ ፓርቲው በማይመለሱት ተመራጮች ፋንታ በ1999ዓ.ም የስራ ዘመን ዳግም ምርጫ (Recall) የማድረግ ስራ በአፋጣኝ የምንቀሳቀስበት መሆናችንን እንዲረዱ የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግሬስ (ኦብኮ) ያስገነዝባል፡፡...»